የሰ/መ/ቁ. 57100

ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጅማ ቅ/ጽ/ቤት ነገረ ፈጅ - ምህረቱ ቁምላቸው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ አዳለ ሰይድ

2. ፍሮሚሲስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ካቀረበው የቀደምትነት ባለመብት ክርክር ጋር የተያያዘው ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግስት በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ድርሻው እንዲሰጠው በመክሰስ ካስወሰነ በኋላ በአፈጻጸም መዝገብ የ2ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነው ክሊንክ ተሽጦ የአፈጻጸም ድርሻ እንዲሰጠው በታዘዘው መሠረት ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ገዢ ባለመቅረቡ የፍርድ ባለመብት /1ኛ ተጠሪ/ ንብረቱን ለመረከብ ጥያቄ አቅርቦ እያለ የአሁን አመልካች ጣልቃ ይግባ፡፡ የአሁን አመልካች በ09-2-2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ 508,564.67 ብር የግብር እዳ ከአፈጻጸም ተከሣሽ /ከአሁን 2ኛ ተጠሪ/ ላይ ስላለን በግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት የቅድሚያ መብት ስላለን የቅድሚያ መብታችን እንዲከበር የሚል ነበር፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች /የአሁን አመልካች/ ከላይ እንደተመለከተው ያመልክቱ እንጅ በአዋጅ ቁ. 286/2002 አንቀጽ 78/1/ መሠረት የባለዕዳውን መያዝ የሚችለው ንብረት አፈጻጸም ላይ ከሌለ እና በዋስትና ያልተያዘ ከሆነ በመሆኑና ከላይ የተጠቀሰው ንብረት ደግሞ በአፈጸጸም ላይ ስላለ የጉምሩክ ጽ/ቤት የቀደምትነት መብት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ብሎ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት አጽንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን በቀን 08/10/2002 ዓ.ም በ2 ገጽ በተጻፈ ማመልከቻ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት አመልካች ለግብር ዕዳ ሲጠየቅ ዋስትና ከተሰጣቸው አበዳሪዎች /ባንኮች/ ተከትሎ የቅድሚያ መብት

ያለው ስለመሆኑ እየታወቀ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለውና በሶስተኛ ወገን የሚገኙቱን ንብረቶች ለማስለቀቅ የተደነገገውን የአዋጁን አንቀጽ 78/1/ በመጥቀስ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ 1ኛ ተጠሪ በቀን 20-4-2003 ዓ.ም በ3 ገጽ እና 2ኛ ተጠሪ ተወካይ በቀን 20-4-2003 ዓ.ም በ2 ገጽ በመጻፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰጡት መልስ ፍሬ ሃሣብ በአጭሩ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ጥያቄ የዘገዬና ንብረቱንም በጊዜያዊነት እንዲያስተዳድር ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ የቀረበ ከመሆኑም በላይ የቀድምትነት መብት አይገባውም የሚል ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች አቅርቦት የነበረው የቀደምትነት መብት ውድቅ ተደርጐ የተወሰነው ውሣኔ አግባብ ባለመሆኑ ተሽሮ የአመልካች የቀደምትነት መብት እንዲከበር በማለት መልሷል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

በግራ ቀኝ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል አመልካች በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት በሌላው ሰው ገንዘብ ጠያቂነት በተያዘ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት አለው ወይስ የለውም የሚል ጭብጥ በመሆኑ ከዚሁ አኳያ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሁለተኛ ተጠሪ /ፎሮምሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር/ በገንዘብ ጠያቂነት ወይም ድርሻውን ለማስከራል እንደሆን አላከራከረም፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ /ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላይ/ ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ በሚመለከተው ንብረት ላይ ቀድሞ በዋስትና ያልተሰጠው ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡

ይሄንን መሠረታዊ ሃሣብ ይዘን የአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

“ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ተከፋይ ከሚሆንበት አንስቶ ተከፍሎ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሃብት ላይ  ባለስልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች ዕዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡” የሚል ነው፡፡

ከዚህ አንቀጽ በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው ከአመልካች ሊቀድም የሚችለው በዋስትና ቀድሞ የተያዘ ከሆነ ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በተመለከተው አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 78/1/ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነቱን ስንመረምር የግብር ከፋይ ንብረት የሆነ በሌላ ሶስተኛ ወገን ሲገኝና በግብር አስገቢው ባለስልጣን እንዲያስረክበው ሲጠየቅ የማስረከብ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑና የማያስረክብበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለው በአፈጻጸም ላይ ስለመሆኑ በመግለጽ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ይሄ አንቀጽ ከተያዘው ጉዳይ ጋር በቀጥታ አግባብነት ያለው ባይሆንም አንቀፁ ሊደነግግ ያሰበው ንብረቱን ለመረከብ ሲፈልግ መከተል ያለበትን ስነ ሥርዓት ከመደንገግ አኳያ በመሆኑ የቀደምትነት መብትን ቀሪ የሚያደርግ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት አመልካች ያቀረበው የቀድምትነት መብት በዚሁ አንቀጽ መሠረት ታይቶ መወሰን ሲገባው ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን የአዋጁን ሌላ አንቀጽ በመጥቀስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉና የይግባኝ ሰሚውም ፍርድ ቤት ይሄንን ሣያስተካክል ውሣኔውን ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግስት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 10/86 በቀን 18-2-2002 ዓ.ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 89407 በቀን 05-9-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የጠየቀው የግብር ዕዳ በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት ከአንደኛ ተጠሪ የቀደምትነት መብት አለው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ